# አንበሣውን አትንኩ !!!!

**Tedla Asfaw**

የኢትዮጵያ  ጥቁር አንበሳ የጥቁሮች ነፃነት !!!!!

በመጀመሪያ የአንድነት ታላቅ መናፈሻ አሳምሮ ላዘጋጁት ጠቅላይ ምኒስትር ዐቢይ አህመድ በጊዜው አድናቆቴን  በጀርመን አማርኛ የአድማጮችአስተያየት መነበቡ ይታወቅልኝ።

ዐለም በቻይናው ተዉሀሲ ብዙ መቶሺ ህይወት ጥፋትና ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዉድመት ብሎም ኢትዮጵያን ለረሀብ ያጋልጣል እየተባለ ባለበት ሰዐት "ኢትዮጵያን የቸገራት ብልፅግና እንጂ አንበሳ አይደለም" የሚል በድህረ ገፅ ከብልፅግና ፓርቲ የወጣ መልዕክት አነበብኩኝ።

አዎ ኢትዮጵያ እራስዋን መመገብ የማትችል ብዙ
ለዕርሻ የሚሆን መሬት ና ብዙ ወንዞች ያሉት ሀገር ናት። ሆድ ሳይሞላ ብልፅግና በኢትዮጵያ አይመጣም።

ኢትዮጵያ ስንዴ ዘይት ልክ እንደ ነዳጅ በዉጭ ምንዛሪ የማስገባት አቅማችን በከቻይና በመጣው ተዉሀሲ ምክንያት  በመንኮታኮቱ  በይበልጥ ለከፍተኛ ረሀብ አጋልጦናል።

ኢትዮጵያን ከባዕድ ሀገራት ወረራ እየተከላከለ የኢትዮጵያን ሀብት  ያስረከበን በነገሥታቱ ታሪክ የሚታወቀው አንበሳ በቅርቡም ከጣሊያን የተፋለመው የጥቁር አንበሣ ወጣት አርበኞች የኢትዮጵያ ምልክት ነው። ለደቡብ አፍሪካም ነፃነት ትግል የጥቁርግስላ ና አንበሳ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርግዋል።

 የአንበሶቹን ግቢ በ ህንድ ፒኮክ ማስጠበቅ የኢትዮጵያን የነፃነት ረዥም ተጋድሎ ማንኳሰስ ይሆናል። አቶ አንበሴን በአቶ ፒኮክ መለወጥም ስንዴ አይሆንም።

የኢትዮጵያ ኀዳሴ ግድብ ላይ የኢትዮጵያ አንበሳ ወይስ የህንድ ፒኮክ ቢደረግ ይሆን ግብፅ የምትደነግጠው ??
ከብልፅግናው በፊት የኢትዮጵያ ህልውና ለማስጠበቅ ያለፉት ኢትዮጵያዉያን ምልክት የሆነዉን አንበሳ ባናጣጥለው ይሻላል።

ይሄ የቻይና ተዉሀሲ ያስተማረን ቢኖር ነፃ ሀገር ለጥቁር አፍሪካዉያን ያላቸው የመጨረሻ ተስፋ ነው።
አፍሪካን ለአፍሪካዉያን ለማድረግ የተዋደቁትን የጥቁር አንበሳና ግስላ በ በቻይና ጭምብል ሆነ በህንድ ፒኮክ መቀየር እራስን ማዋረድ ነው።